# እግዚአብሔር የራሱ ተርጓሚ ነው

የሰማይ አባታችን ሆይ፤ ከአንተ ዘንድ የሆነ ቃል ማንም ሰው በየትኛውም ጊዜ ሊሰራው እና ሊለው ከሚችለው በላይ ነውና፤ ሰዎችም ሊያዩህ በመጠባበቅ ላይ ናቸው። ጓግተው የሚጠባበቁ በመኖራቸውም እናመሰግንሃለን፤ አንዳች ነገር ይሆናል ብለው በመጠበቅ ናቸውና። ህዝቡም አንዳች ነገር እንደተጠማ፤ ጥልቁ ወደ ጠለቀው ይሰባልና፤ ለዚያ ፍለጋ መልስ ያለው ጠለቅ ያለ ነገር ሊኖር ግድ ነው። ዛሬም እዚህ የተገኘነው ለዚህ ነው፤ ምክንያቱ በአገልጋዮች ልብ፤ እና በህዝቡ የነበረ፤ በረከት እና ሞገስ ከአንተ ዘንድ እንድንሻ ትሰበሰበን ዘንድ ነው፤ ህመምተኛውን ፈውሰህ የጠፋውን የምታድን፤ ቃልህም የምትገልጥ መሆንህን እምነናል።

2 የሰማይ አባት ሆይ፤ ይሄን ትሰጠናለህ ብለን ከማታ እስከ ማታ በትህትና አንተን እየተጠባበቅን፤ እንጸልያለንና። የዚህን ዓይነት የ—የ የመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ይኑር፤ ሰው ሁሉ ከእግዚአብሔር በቀር በዙርያቸው ላለ ነገር ሁሉ መታወር ይሁን። በህዝቡም መካከል፤ እግዚአብሔርን የመጠማት ታላቅ ልመና፤ ይኑር፤ በምድሪቱ ዙርያ ሪቫይቫል እስኪሆን እና ቸርቾች ሁሉ በሰዎች እስኪጨናነቁ ድረስ ይሁን፤ ሐጥያተኞች ለእግዚአብሔር ምሕረት በታላቅ ድምጽ እስኪለምኑ ድረስ፤ እና—እና መንፈስ ቅዱስ ህመምተኞችን ይፈውስ፣ ጉንድሾችን ያራምድ፣ ሙታንን ያስነሳ፤ በቃልህ ተስፋ የተሰጡት ሁሉ ፈጽም።

3 ና፤ ጌታ ኢየሱስ፤ ቃልህም ፈጽም። ዛሬ ምሽት ናልን። ተስፋ ቃልህ እንደማይወድቅ፤ ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከ ዘለአለም ድረስ፤ ያው እንደሆንክ እናምናለን። ሰማይና ምድር ያልፋል ቃልህ ግን አያልፍም። ማስተዋላችን ይከፈት። መንፈስ ቅዱስ ይምጣና አዳሪ መሬቱን ያበጅልን። ግንዛቤአችን ዛሬ ማታ ለእግዚአብሔር መንፈስ እና ኃይል ይከፈትለት፤ የተሰፋ ቃሉን በእኛ በኩል ይገልጸው ዘንድ። በኢየሱስ ስም ጸልየናል። አሜን።

4 አሁን በዚህ ምሽት፣ ርዕሱን ማወቅ ለምትፈልጉ፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛው ጴጥሮስ መጽሐፍ ላይ እንመልከት፤ በቅዱስ ቃሉ ላይ ለጥቂት ደቂቃ መግቢያ እንዲሆነን፤ ከ15ኛው ቁጥር እንጀምር።

> **ከመውጣቴም በኋላ እነዚህን ነገሮች እንድታሰቡ በየጊዜው ትችሉ ዘንድ እተጋለሁ።**
>
> **በብልሃት የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል፤ የግርማው የዓይን ምስክሮች ሆነን፤ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ።**

5 እቺን እወዳታለው፤ “የዓይን ምስክሮች።” ተረት አይደለም። ስለምናወራው ነገር ምስክር ነን።

> **ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሎአልና፡ ከገናናው ክብር ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ፤ በእርሱ ደስ የሚለኝ፡ የምወደው ልጄ ይህ ነው።**

**እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋር ሳለን፤ ይህን ድምፅ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን።**

**ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤ ይህን ቃል** እየጠነቀቃችሁ **መልካም ታደርጋላችሁ፤ በጨለማ ሰፍራ... እንደሚበራ መብራት፤ ምድርም እስኪጠባ ድረስ፤ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ፤**

**ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤**

**ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።**

6 ጌታ በተነበበው ቃል በረከቱን ይጨምር። አሁን እንደ ርዕስ የምጠቀመው፤ **እግዚአብሄር የራሱ ተርጓሚ ነው፥** የሚለውን ይሆናል።

7 ያለነው ግራ በሚያጋባ ዘመን ነው። ሴቱም ወንዱም ማድረግ ያለበትን በማያውቅበት ዘመን እንገኛለንና። በአጠቃላይ፤ በተወሳሰበ—ሁኔታ የደረስን ይመስላል። እያንዳንዱ ነገር፤ የምንረዳበት መንገድ የበዛ ይመስላል። ይህን የሚያደርገው፤ ሰይጣን ነው።

8 አሁን እግዚአብሄር፤ ሰዎችን የሚፈርድበት መስፈርት ካልኖረው በቀር፤ በጽድቅና፣ በቅን ሊፈርድባቸው አይችልም። መጽሐፍ ቅዱሰም ሲናገር ሰውን ሁሉ በኢየሱሰ ክርሰቶሰ እንደሚፈርድ ነው። ኢየሱሰ ክርሰቶሰም ቃል ነው። በቅዱሰ ዮሐንሰ 1ኛው ምዕራፍ ላይ፤ እንዲህ ይላል፡

**በመጀመሪያ ቃል ነበረ ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።**

**ቃልም ሥጋ ሆነ፤ በመካከላችንም አደረ፤...**

9 ዛሬ እኛ፤ ሁላችንም የባሕርዩ ማሳያ ብቻ ነን። በእግዚአብሔር ዘንድ፤ አምላክ... በመጀመሪያ አምላክ አልነበረም፤ "ዘላለማዊ" ብቻ ብለን እናጠራዋለን። እሱ አምላክ አልነበረም፤ ምክንያቱም ቃሉ (የእንግሊዝኛው ቃል) **አምላክ** ማለት "የሚመለክ ነገር" ማለት ነው፤ የሚያመልከው ግን አልነበረም። ስለዚህ እርሱ፤ ዘላለማዊ—የዕውቀትና ችሎታ ሁሉ ምንጭ ነበር። እናም በዚህ ሁሉ የዕውቀት ምንጭ ውስጥ አቶም ቢሆን ሞለኪውል፤ ወይም ሌላ ነገር አልነበረም፤ የትም ቦታ ብርሃን፣ ኮከብ፣ ጨረቃ፣ ምንም አልነበረም። ይህ እንደ አምላክ የምናውቀው፤ እግዚአብሔር፤ (መጀመርያ የሌለው፣ መጨረሻም የሌለው)፤ ዘላለማዊው ታላቅ መንፈሰ ያኔም ነበረ። በእርሱም ዘንድ መገለጫዎች ነበሩት፤ አምላክ የመሆኑ መገለጫዎች፤ ቀጥሎም አባት የመሆኑ መገለጫ፣ ልጅ የመሆን መገለጫ፤ የአዳኝነት መገለጫው፣ ፈዋሽ የመሆን መገለጫዎች። እነዚህ ሁሉ መገለጫዎች በእርሱ ዘንድ ነበሩ። እና አሁን... ያኔም ጀምረው እየታዩ የነበሩት እነዚህ ነገሮች የተገለጡ መገለጫዎቹ ናቸው።

10 **መገለጫዎች፤** ማለቴ “ሐሳቦቹ።” ቃል—ማለት “የተገለጸ ሐሳብ” ማለት ነው። ስለዚ ያኔ በሐሳቡ የነበረው ይህ ነው። እና፤ “ይህ ይሁን” ሲል፤ ይሆን ነበር። “ይህ ይሁን ሲል፤” ይሆናል።

11 አሁንም፤ እናንተ ክርስትያኖች አስታውሱ፤ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት በሐሳቡ ነበራችሁ። ስለዚህ እናንተ የሀሳቡ መገለጫ ናችሁ። ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እንኳን፤ ቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ፤ (አሜን) በክርስቶስ ነበራችሁ። ስለዚህ፤ አያችሁ፤ ይህ የሱ እንድትሆኑ ያስችላችኋል። ስለዚህ መላ ፍሬ ነገሩ፤ አምላክን፤ ማየት እንዲቻል፣ መዳሰስ እና—ወዘተ እንዲቻል እራሱን የሚጨበጥ አካል ማድረጉ ነው። በአጠቃላይ፤ አምላክ ይህ ነው።

12 ሰዎች ሲናገሩ “ትርጓሜው… ” ይላሉ፤ ባለፉት ቀናት እዚህ ስብሰባ ላይ፤ አንድ ሰው ያለኝን ተናግሬዋለሁ፤ እንዲ አለኝ፤ “ወንድም ብራንሃም፤ አተረጓጎም ተሳስተሀል። በትክክል አልተረጎምከውም።”

13 አሁን ወደ ሜቶዲስት ሲሄዱ፤ “ባፕቲስቶች በትክክል አይተረጎሙትም።” ሲሉ እንሰማለን፤… ባፕቲስቶችም “ጴንጤቆስጣሎች አይችሉም” ይላሉ። ጴንጤቆስጣሎችም “ዋንነሶችን አይችሉም” ይሏቸዋል። ዋንነሶቹም “አስምብሊዎቹን አይችሉም” ይሏቸዋል። አንዱ ለሌላው አልቻለም ይባባላሉ።

14 እንዲተረጉምለት አንድም ሰው አይፈልግም። እግዚአብሔር የራሱ ተርጓሚ ነው! የራሱም ትርጓሜ ያደርጋል። እግዚአብሔርን ለመተርጎም የሚችል ሰው ማነው? እግዚአብሔር የራሱ ተርጓሚ ነው።

15 አሁን እዚህ ጴጥሮስ በሚናገርበት ስፍራ፤ በመጀመርያ እግዚአብሔር፤ “ብርሃን ይሁን” ሲል እናያለን፤ ብርሃንም ሆነ፤ ትርጓሜውም ይሄን ነው። እግዚአብሔር አንዳች ነገር ተናግሮ ያለው ሲሆን፤ ቃሉ እውነት እንደሆነ የእግዚአብሄር ትርጉሙ ያ ነው። አያችሁ? እሱ “ብርሃን ይሁን፡” ሲል፤ ብርሃን የሚባል ነገር ከመኖሩ አስቀድሞ፤ በሐሳቡ ውስጥ የነበረ ነገር ነው። “ብርሃን ይሁን” ባለ ጊዜ፤ በሰማያት ብርሃን ፍንትው አለ፤ ትርጓሜውም መሆኑ ነው። እግዚአብሔር የተናገረው ስለሆነለት፤ ማንም ይሄን ሊተረጉም አይገባም። እግዚአብሔር ተናግሮ የተናገረው ሲፈጸም፤ የቃሉ ትርጉም ማለት እንዲህ ነው። ለምን ሰዎች ይሄን ማየት አቃታቸው? ህዝብ ይሄን ማየት ለምን አቃተው?

16 እግዚአብሔር ቃል ሲገባ እንዲሁም እግዚአብሔር ሲናገር… በመጀመርያ—በዘፍጥረት፤ ቃሉን፤ ከጅማሬ እስከ ፍጻሜው ድረስ በየደረጃው ለእያንዳንዱ ዘመን ከፋፍሎ አስቀምጧል። በእነኚህም ዘመናት ሁሉ፤ ቤተክርስትያኒቱ፤ እነዚህን ነገሮች ከባህልና፤ ከብዙ ነገሮች ጋር ትደበላልቀዋለች፤ እግዚአብሔርም ሁሌ፤ በብሉይ እና በአዲስ ኪዳን፤ ነብያትን ወደ ዐውዱ ይልካል! የጌታ ቃል ወደ ነቢዩው ይመጣል። እንዴት ያደርገዋል? የእግዚአብሔርን ቃል ይገልጣል። ትክክል ወይስ ስሕተት መሆኑን የሚያሳይ፤ የእግዚአብሄር መገለጥ። ቃል እራሱን ይተረጉማል፤ ማንም ሊተረጉመው አያስፈልግም። እግዚአብሔር ቃል ገብቶ ወድያው ይፈጸማል!

17 ስለእሱ የማይሆን ነገር ቢነገር ምን ይጠቅማል? (እግዚአብሄር የገባውን ቃል የሚፈጽም ሆኖ ሳለ) ይሄኛው ትርጉም ልክ አይደለም ለማለት የሚደፍር ሐጢያተኛው ሰው ማን ነው? ስለራሱ የራሱ ትርጉም የሚተረጉም፤ ራሱ

እግዚአብሔር ነው። እንዲተረጒምለት ማንም ሰው አይሻም፤ ይሆናል ያለውን ቃል በመፈጸም እራሱን በራሱ ይተረጒማል።

18 ኦ፤ ቤተክርስትያን ይሄን ተረድታ ለእያንዳንዱ ዘመን የተመደበውን ቃል ማየት በቻለች! (በሰባቱ አብያተ ክርስትያናት ዘመን ሳይቀር) በሌሎች ዘመናት ሁሉ፤ እግዚአብሔር ወደ ዐውዱ ልኳል። ለማድረግ ቃል የገባቸው ነገሮች ሁሉ ገልጧቸዋል። እያንዳንዷ፤ ሳትፈጸም የቀረች አንዳች ነገር የለችም። በትክክል! አደርጋለሁ ያለውን፤ አድርጓል።

19 ምክንያቱም እግዚአብሔር በኢሳይያስ፤ ሲናገር፤ "ድንግል ትፀንሳለች አለ፤" ጸነሰችም። አሁን ያንን፤ ማን ነው—ማን ተረጎመው? እግዚአብሔር ተረጎመው። "ድንግል ትፀንሳለች ፣" አለ፤ ጸነሰች። አሁንስ እናንተ፤ ምንም... አትችሉም... ስለዚህ ነገር አንዳች ነገር ማለት አይቻልም፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አለ ፈጸመችው። ቤተክርስቲያ ግን ያኔ ይሄን ለማየት በጣም ታውራ ነበር። እያችሁ፤ የራሳቸው አመለካከት ነበራቸው። ከጠበቁት እጅጉን—የተለየ ነበር።

20 ጴጥሮስ ወደኋላ ተመልሶ ሲጠቅሰው፤ "እግዚአብሔር ክርስቶስን በቃሉ ሲገልጥ 'ይህ የምወደው ልጄ ነው'" ብሎታል ይለናል። አማኞች በዚያ ቆሟል። ክርስቶስም የእግዚአብሔር ትረካ ነበር። ክርስቶስ ቃል ስለሆነ፤ ክርስቶስን ሁልጊዜ በቃሉ ይተርከዋል። ሁል ጊዜ ይገለጣል።

21 ... በኖህ ዘመን ሲናገር፤ ክርስቶስ በኖህ ውስጥ ነበረ። ይሄን ታምናላችሁ? ኖህ "ሊዘንብ ነው። ዝናብ ይመጣል፤ ምድርም ትጠፋለች" አላቸው። ዘነበም። ሌላ ትርጉም አይፈልግም። እግዚአብሔር፤ በኖህ ውስጥ ሆኖ፤ "ይዘንባል" ስላለ፤ ዘነበ። እሱ ነብዪ ነበር፤ ማስረጃውም የተናገረው ሆኖለታል። ስለዚህ ይህን ሊተረጉሙ አይገባም።

22 ምናልባት በሱ ዙርያ፤ አንዳንዶች፤ "ይህ ሰው የሚናገረው አያውቅም" ብለውት ይሆናሉ።

23 እግዚአብሄር የገባው ቃል ግን፦ "ከእናንተ መንፈሳዊ ወይም ነቢይ የሆነ አንድ ቢኖር፤ የተናገረውም ነገር ቢፈጸም፤ ሰሙት።" ትክክል፤ እውነት ስለሆነ። በቃሉ መሠረት መሆን አለበት። ኖሳም ቃልን መሠረት ያደረገ ነበር። ይዘንባል ብሎ ትንቢት ሲናገር፤ ዝናብ ዘነበ። ያንኑ ስለተፈጸመ፤ ሌላ ትርጉም አያስፈልገውም።

24 ኢሳያስም "ድንግል ትጸንሳለች" አለ፤ ጸነሰች። አሁን ይሄ፤ በጣም ያልተለመደ ነበር። ምክንያቱ፤ ድንግሊቱ ከመጸነሷ ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ ነው፤ እያችሁ።

25 እስከ ባልዋ ዮሴፍ የሚባለው መልካም ሰው ድረስ፤ እንግዳ ነገር ነው፤ "ጻድቅ ሰው ሆኖ በማሕበረሰቡ ዘንድ መቀጣጫ ሊያደርጋት አልወደደም... " ይህ መልካም ሰው፤ የማርያም ባል እንዲሆን በታጨ ጊዜ፤ ዮሴፍ ምን ተሰምቶት ይሆን።

26 እጮኛ ነበራት። ያኔ ይሄን መተላለፍ ማለት፤ ዝሙትን እንደመፈጸም ነው። ደግሞም በትክክል፤ ለዮሴፍ፤ ማርያም ስለሐጢያትዋ መሸፈኛ እንድትጠቀምበት የፈለገችው ይመስላል፤ ወይም ስለ ጥፋትዋ ጋሻ ለማድረግ፤

ገና ያላገባች፤ የታጨች ብቻ ስትሆን፤ እናት ሆና ስለተገኘች። እንዲህ ያለ ማጭበርበር፤ በሕጉ፤ እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ይወገራል፤ ግድ ነው።

27 ባለቤትዋ፤ ዮሴፍ ግን፤ ጻድቅ ሰው፤ እጅግ ጻድቅ ሰው ሰለ ነበር። እግዚአብሄርን ያምናል። በእነዚያ ፍቅር በተሞሉ፣ ለሰላሳና ትልልቅ ዓይኖቿ እያየችው፤ እንዲህ ስትለው፦ “ዮሴፍ፤ የመላእክቱ አለቃ ገብርኤል ወደ እኔ መጥቶ፤ ወንድ ሳታውቂ ታረግዢለሽ ብሎ ነገረኚ።”

28 አሁን ዮሴፍ፤ እንዲህ እንደምትሆን ነብዩ መናገሩ ቢመረምርና፤ ቅዱስ ቃልን ዞሮ ቢያይ ኖሮ! እግዚአብሔር ቃሉን መተርጎሙ ብቻ ነው! እያችሁ? ነገር ግን እጅግ ያልተለመደ ነበር።

29 በየትኛውም ዘመንም እንዲሁ ነው። የእግዚአብሄር ቃል ለህዝቡ እንግዳ ነው፤ እጅግ ያልተለመደ። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ያልተለመደውን ያደርጋል። እግዚአብሔር ባለበት ቦታ ሁሉ ያልተለመደ ነው። መሆን አለበት ብለው በሚያስቡት መንገድ ነግሮችን ስለሚረዱ፤ ከዓለም ሥርዓቶች ሁሉ ጋር ይቃረናል። ጌታ ግን መጥቶ ያልተለመደውን ማድረጉ ይቀጥላል።

30 “ይህች ድንግል እንዴት ፀነሰች?” ቅን ስለነበረ ፣ በዚህ ጉዳይ እግዚአብሔርን ጠየቀ።

31 እግዚአብሔርም በሕልም ተናገረው፤ እንዲህም አለው፦ “የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ ፥ ሚስትህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ፤ የሆነው በዚህ መልኩ ነው። እግዚአብሔር አጽልሎላታል። በእርሷ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና።”

32 እግዚአብሔር ከዮሴፍን ጋር እንዴት እንደሰራ አስተውላቿል? በሕልም በኩል ፤ በሁለተኛው መንገድ ነው። አሁን ህልሞች፤ እንዳሉ እናውቃለን፤ በሕልሞች እናምናለን። እኔም በሕልም አምናለሁ። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ሰዎችን በሕልም ሲናገራቸ... ቆይቷል። ሕልሞች ግን ሁለተኛ ደረጃ ናቸው፤ እያችሁ፤ ካልተተረጎሙ እውነትም ሰህተትም ሊሆኑ ይችላሉ። ለሱ ግን ትርጉም አያስፈልገውም። በዚያ ዘመን ሊተረጉም የሚችል ነብዩ ምድሪቱ ላይ ሰላልነበረ፤ ዮሴፍን በቀጥታ የተናገረው እግዚአብሔር ነበር። ለአራት መቶ ዓመታት ገደማ ነብዩ አልነበራቸውም። ሰለዚህ እግዚአብሔር ስለ ልጁ ደህንነት እንዲጠነቀቅ፤ ሁለተኛው አማራጭ፤ ዮሴፍን ያለ ምንም ትርጉም በሕልም በኩል መናገር ነበረበት። እንዲህ አለው፤ “ሴቲቱ ልክ ናት። በውስጧ የተጸነሰው ይህ ቅዱስ ነገር ከእግዚአብሄር ነው።” ምንም ትርጓሜ አላስፈለገውም።

33 ለቅኖችና ለእውነተኛ ልቦች፤ እግዚአብሔር እራሱ ይተረጉምላቸዋል። ሚስጢራዊ የሆኑ—ነገሮችን እየጠበቃችሁ ያላችሁ ሴቶች እና ወንዶች፤ ካመናችሁና፤ ቅኖች እና ልባሞች ከሆናችሁ፤ እግዚአብሄር ለእናንተ የሚተረጉምበት መንገድ አለው። ከሁሉ በፊት ግን፤ ቃል ኪዳን እንደሆነ መርምሩ። ዮሴፍ ከባህላዊ ነገሮች ወጥቶ መለሰ ቢል ወደ መጽሓፍ ቅዱስም ቢመለስ፣ ኢሳያስ ታረግዛለች ማለቱን ፤ ቢመረምር።

34 ሰለ አወላለዱና፤ በቅዱስ ቃል ሰለሱ የተነገሩ ነገሮች ሁሉ፤ “በነብያት አፍ፤” ሰለሱ የተባሉ ነገሮች ቢመረምር፤ ጴጥሮስ እንዳለው ማንም ሰው የግሉ ትርጓሜ የመስጠት መብት የለውም። እግዚአብሔር ይሆናል ያለው ብቻ

ነው የሚሆነው። ለዛው ዘመን የተነገረውን የእግዚአብሔርን ኪዳን መተረኪያ ነበር። እግዚአብሔር ተናገረ፤ እንዲሁ ሆነ፤ አከተመ።

35 ኢየሱስ በምድር ሳለ፤ አገልግሎቱን መረዳት ባለመቻላቸው፤ እንዲህ አላቸው... በብዙ ክስተቶች የተሞላ፤ እጅግ ድንቅ፤ ማለት፤ አሰደናቂ ቢሆንም። ሊረዱት አልቻሉም፤ (አልቻሉም)። “ቅዱሳት መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ!” አላቸው፤ (ጮኬ፤ እንዳላደነቆርኳችሁ ተሰፋ አደርጋለሁ።) “እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና፤ እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው።” አያችሁ? “ማን እንደሆንኩ የሚናገሩ ናቸውና።”

36 አያችሁ፤ ያቺ ቀን የእግዚአብሄር (የአማኑኤል) ከእኛ ጋር፤ የእግዚአብሔር መገለጫ ቀን እንድትሆን፤ ጌታ ቃሉን መድቧል፤ “ሰሙም ድንቅ፣ መካር፣ የሰላም አለቃ፣ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት። ሰሙም **አማኑኤል** ይባላል። ‘እግዚአብሔር ከኛ ጋር’” አምላክ በዳዊት ውስጥ ነበረ። አምላክ በሙሴ ውስጥ ነበረ። አምላክ! በየዘመኑ እራሱን እየተረከ፤ አምላክ በሁሉ ነበረ። ይህች ዘመን ግን፤ “ድንግል ጸንሳ ወንድ ልጅ ልትወልድ ነው፤ እሱም እግዚአብሄር ከኛ ጋር ይባላል።”

37 የሰቀሉትም ለዚህ ነው፤ እራሱን አምላክ በማድረጉና፤ ሰንበትን በመሻሩ። በሰንበት ላይ ጌታ ነበር—አምላክም ነው። (ምንም ሰው እና ነብዪ ቢሆንም) ዝም ብሎ ተራ ሰውና ተራ ነብዪ ግን አልነበረም፤ ነገር ግን አምላክ-የሆነ ነብዪ ነበር። እንዲህ ያደርጋል ብሎ እግዚአብሄር ሰለሱ እንደተናገረ፤ የቃል መደምደምያ ነበር። “ከእናንተ ሰለ ኃጢአት እኔን የሚወቅሰኝ ማን ነው? ቅዱሳት መጻሕፍትን ትመረምራላችሁ! አላቸው፤ የዘለአለምን ህይወት የምታገኙባቸው ይመስላቿል፤ እነርሱ ግን ሰለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው።” ሰለ ወጎቻቸው ግን፤ ኑሮአቸው በሌላ ዘመን ብልጭታ ነበረ።

38 ከጥቂት ሳምንታት በፊት፦ “**በብልጭታ መኖር**” ብየ ሰብኬአለሁ። ብልጭታ፤ ጸሐይ የምታንጸባርቀው፤ ሀሰተኛ “ነጸብራቅ” ነው። የትኛውም የሌላ ዘመን ብልጭታ ሐሰተኛ ነጸብራቅ ነው ህዝቡ ባለፉት አመታት በሆኑ ነገሮች ውስጥ እየተጓዘ ይገኛል። ሉተራን በሉተራን ብልጭታ ይራመዳሉ። የሉተር ብርሃን በዘመኑ መልካም ነው፤ ዌሰሊም በዘመኑ መልካም ነበር፤ የጴንጤቆሰጤም ዘመን መልካም ነበር። በመሰላል ወደ እየወጣን፤ አሁን ያለንበት ዘመን ሌላ ነው! ወደ ኋላ ማየት አንችልም፤ እየተጓዝን፣ ጉዞ፤ ላይ ነን።

39 በነገሮች ሁሉ ሰናርፍ፣ ሁሉን የደረሰንበት ይመስለናል፣ በወጎቻችን እንጠቀለላለን፤ ለራሱ ዘመን ቢሆን መልካም፤ ነገር ግን ጉዞው ይቀጥላል! ሰለዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት መርምሩና የዛሬውን ኪዳን አሰተውሉት፣ ከዚያ በኋላ ያለንበትን እናውቃለን፤ ከዛ በኋላ የት እንደቆምን መናገር እንችላለን።

40 መጽሐፍ ቅዱሰን ተመልክታችሁ፤ ሉተርን፤ በሰርዴሰ—ዘመን ማየት ትችላላችሁ፤ የተገባው ኪዳን በግልጽ ማየት ትችላላችሁ። የወጣው ጋላቢ ምን ዓይነት እንደነበረ አሰተውሉት፤ እሱን ለመግጠም የወጣውም እዩት፤ በትክክል፤ “የሰው ልጅ ብልሃት” ተሃድሶ። ዌሰሊን፤ ሌሎችንም ተመልከቷቸው። ወደ ጴንጤቆሰጤ ዘመን እየወረደ፣ በዛው ዘመን አልፎ፤ እንዴት እንደተጓዘ

ተመልከቱት። ቅዱሳት መጻሕፍትን ፈትሹና የደረስንበትን እዩ። ኢየሱስ፦ “ቅዱሳት መጻሕፍትን መርምሩ!” ያለበት ምክንያት ይሄው ነው።

41 የደረስንበትን እዩት! ያለንበት የእግዚአብሔር ልጅ መምጣት ዘመን እንደሆነ አምናለሁ። በየትኛውም ቅጽበት ሊመጣ በሚችልባት—ዘመን እንዳለን አምናለሁ። እኛ ያለንበት ጊዜ የዓለም የመጨረሻ የታሪክ ምዕራፍ ውስጥ እንደሆነ፤ ቅዱሳት መጻሕፍት ማወጃቸውን አምናለሁ። ነገሮች ቦታቸውን ሲይዙ ይታየኛል። ይህ የአብያተ ክርስትያናት ህብረት ቸርቾችን፤ ወደ አውሬው ምልክት ሲመራቸው አያለሁ። ሮማን ኢምፓየርና፤ ሌሎቹ ምን እያደረጉ እንዳሉ አያለሁ። ሁሉም መብራቷን ለማጥፋት፤ ወንጌልን ለመዝጋት፤ ሁሉም አንድ ሲሆኑ አያለሁ። ሰው ሁሉ በብርሀናቸው ይጓዛል እንዲሁም አባል መሆን ይኖርበታል ካልሆነ ግን ፈጽማችሁ አትጓዙም። አያችሁ፤ በዘመን ፍጻሜ እንገኛለን። እግዚአብሔርን ከመደገፍ እና ቃሉን ከማመን በስተቀር የቀረልን ነገር የለም። ቃሉ ሁል ጊዜ ትክክል ነው።

42 የሎዶቅያ ቤተክርስትያን ዘመን፤ ከነዚህ ሁሉ ተለይታ፤ ክርስቶስ ከቤተክርስትያን ውጭ፤ በውጭ ቆሞ፤ እንዲያንኳኳ፤ የተደረገባት ብቸኛዋ የቤተክርስትያን ዘመን ናት። ምን ተፈጥሮ ነው? ወደ ውጭ ያሰወጣው የዓለም አብያተክርስትያናት ሕብረት ነው ። መጽሀፍ ቅዱስ ወደ ውጭ እንደሚወጣ ተናግሯል፤ እሱም በሰተውጭ አለ። ምን ዘጉ? ቃሉን ዘጉ። ቃል እሱ ነው፣ ሁሌም ቃል ነበር፣ ዛሬም ቢሆን ቃል ነው! እሱ ቃል ነው።

43 መጽሐፍ ቅዱስ “ቃሉ ሰለታም ፣ ከሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ፣” “የልብ ሰሜትን እና ሀሳቦችን ይመረምራል” ይለናል፤ ዕብራውያን፤ ምዕራፍ 4። ቃል! በዚያ በተናገራቸው ዕለት ኢየሱስ ማን እንደሆነ ሊያውቁት ይገባቸው ነበር።

44 ያደረገውን ተመልከቱ። በአገልግሎቱ መጀመርያ ቀናት፤ አንድ ቀን ቆሞ ሳለ። ሰምዖን የተባለ ሰው፤ ሰምዖን ጴጥሮስ፤ ወደሱ መጣ። ጴጥሮስም እሱን ባየው ጊዜ—እሱን ሲያይ፤ ኢየሱስ፦ “ሰምህ ጴጥሮስ ትባላለህ የዮና ልጅ ነህ” አለው። (ሙሴ ያለውን ማወቅ ነበረበት፦ “እምላካችሁ እግዚአብሔር እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣል፤ እርሱን ሰሙት።”) እዚህ ጋር ደግሞ ፈጽሞ አይቶት የማያውቅ ሰው፤ “አንተ የዮና ልጅ ሰምዖን ነህ” ይለዋል። ለምን፤ ወድያውኑ ከሱ ውጪ ሌላ እንዳልሆነ... ለመቶዎች ዓመታት ያህል ነቢዪ አልነበራቸውም፣ አሁን ግን ማንነቱን የሚነግረው ሰው ተገኘ። ይሄን መቀበል መቻሉ አይገርምም!

45 ያኔም፤ ፊልፖስ፤ ሄዶ—ናትናኤልን ከዛፍ ሥር አገኘውና ወደ ኢየሱስ አመጣው። ኢየሱስም “እነሆ ተንኮል የሌለበት እሰራኤላዊ” አለ።

እሱም “መምህር፤ ከወዴት ታውቀኛለህ? ” አለው።

46 “ፊልጶስ ሳይጠራህ፤ ከበለስ በታች ሳለህ፤ አየሁህ” አለው።

47 እሱም፤ “መምህር፤ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ! አንተ የእስራኤል ንጉስ ነህ” አለ። ማን እንደሆነ አውቆታል! ሞኑ? ምንም ትርጓሜ አያስፈልገውም፤ ያሕዌ ተናግሯልና!

48 የማያምኑ ሁሉ በዚያ ቆሟል። "ይህ ሰው ቡኤልዘቡብ ነው። የሆነ ነገር አለው—የሚጎትትበት ማታለያ አለው። ይሄ—ይሄ ፋርቱና-ነጋሪ፤ ሌላም ሌላ ነገር" ብለውታል።

49 ኢየሱስ ተመለከታቸውና፤ "ለምን፤ በሰው ልጅ ላይ ቃል ብትናገሩ፣ ይተውላችኋል። መንፈስ ቅዱስ ይሄን ለማድረግ በመጣ ጊዜ፤ እሱን በመቃወም ብትሳደቡ ግን፤ ፈጽሞ ይቅር አይላችሁም፤ በዚህ ዓለም ወይም በሚመጣው ዓለም።" ወደፊት ስለምናያት ቀን፤ ስለ ዘመናችን ትንቢት ነገራቸው። ትላንትናና፣ ዛሬ፣ እስከዘለአለም ድረስ ያው ነውና።

አስታውሱ፤ በሙሴ ውስጥ የነበረው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

50 በዳዊት ውስጥም ኢየሱስ ክርስቶስ ነበር። ዳዊት፡ የእንትና ልጅ... ዳዊት የተናቀው ንጉስ፣ ወደ ተራራው ሲውጣ፣ ስለ ኢየሩሳሌም አለቀሰ፣ ይህ ሌላ አይደለም ክርስቶስ በእሱ ዘንድ እንጂ። ከስምንት መቶ ዓመታት በኋላ፣ የዳዊት ልጅ ወደ ደብረ ዘይት ወጥቶ ኢየሩሳሌምን አያት፣ እያለቀሰ እንዲህ አላት፤ "ኢየሩሳሌል፣ ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ዶሮ ጫጩቶችዋ እንደምትሰበስብ ልሰበስብሽ ወደድሁ፤ አንቺ ግን አልወደድሽም!"

51 ዮሴፍ በታሰረ ጊዜ፤ ያም ኢየሱስ ነበር። ለሰላሳ ብር ያህል በተሸጠ ግዜ፤ ኢየሱስ ነበር። የጶጢፋር ዋና ባደረጉት ጊዜም፤ በፈርዖን ቀኝ ሲቀመጥ። ይሄም ኢየሱስ ነበር። ዮሴፍ ሲነሳ... መለኸት ይነፋል፤ አንድም ሳይቀር ሰው ሁሉ፤ በጉልበቱ ይሰግዳል፤ ይህም ኢየሱስ ነበር። በዮሴፍ በኩል በቀር—ማንም ሰው ወደ ፈርዖን መምጣት አይቻለውም ነበር፤ በኢየሱስ ካልሆነ በቀር፤ ማንም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ አይችልም። በትንቢት ተነግረው የተፈጸሙ ቃላት፤ በጥላ እና በምሳሌ የተነገረ ሁሉ፤ ስለ ኢየሱስ ነው።

52 ኢየሱስ በምድር በነበረ ጊዜ፤ ነብያት ያደረጉትን በተመሳሳይ አድርጓል፣ የእግዚአብሔርን ቃል መፈጸምያው መሆኑ የተረዱትም ስለዚህ ምክንያት ነበር። ሊተረጎም አይገባውም።

53 ናትናኤል ይሄን ሲያይ፤ ወድቆ፣ እንዲህ አለ፦ "አንተ የእስራኤል ንጉስ ነህ፣ የእግዚአብሄር ልጅ፣ የእስራኤል ንጉስ ነህ። ይሄን ሊያደርግ የሚችል ሰው የለም፤ አውቀንሀል።"

54 ኒቆዲሞስ በሌሊት መጣ፤ ለፈሪሳውያኑም ተመሳሳይ ተናገራቸው። ይሁን እንጂ፤ በዓለም አቀፉ ጉባኤ እጅግ የተጠመዱ ስለሆኑ ሊቀበሉት አልተቻላቸውም። "መምህር፤ እኛ... " አለ፤ እነሱ የሚሉትን ነገር ገለጸ፤ ማንን ነው "እኛ"? ጉባኤቸውን ነው! "እግዚአብሄር ከሱ ጋር ከሆነ በቀር፤ እነዚህ ማድረግ የሚቻለው የለምና፤ መምህር ሆነን ከእግዚአብሄር እንደመጣህ እናውቃለን።" እውቅናን ሰጥተውታል፣ አውቀውታል፤ ቢሆንም በነገር እጅግ ተጠመደዋል።

55 አሁንም፤ እግዚአብሄር ላለፉት አርባ ዓመታት ይህችን ምድር በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እናውጧታል። ነገር ግን አሁንም ወንዶችና ሴቶች በተመሳሳይ ወጥመድ ስለተያዙ፤ በሌላ ዘመን ብልጭታ በመኖር ከሱ የራቁ ናቸው። ምንድነው ችግሩ? ሰው ሁሉ ሜተዲስት፣ ባፕቲስት፣ ፕረስቢተርያን፣ ሉተራን፣ ሌላ ነገር መሆን ያምረዋል። አያችሁ፤ ብልጭታ ነው።

56 በሙሴ ዘመን ብልጭታ ይኖሩ ነበር። ምን አለ? እንዲህ አለ... "እኛ የሙሴ ደቀመዝሙርት ነን" አሉ።

57 "ሙሴንስ ባወቃችሁት፤ ታውቁኝ ነበር። ሙሴስ ስለ እኔ ጻፈ!" አላቸው፤

58 ሉተርን ብታውቁት፤ ይሄን ዘመን ባወቃችሁት ነበር! ሜተዲስትንስ ብታውቁ ይሄን ዘመን ባወቃችሁ! ክርስቶስ ስለዚህ ዘመን ጽፏልና! የተፈጸሙት ቃላት በዚህ ዘመን ይፈጸሙ ዘንድ ያስፈልጋልና። የሚተረጒማቸው ሰው አያስፈልጋቸውም፤ እግዚአብሔር እራሱ ይተረጒማቸዋል። እግዚአብሄር እራሱን ይተረጒማል፤ መተርጎም የሚችል እሱ ብቻ ስለሆነ። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ሁልጊዜ እሱ ያለውን ይገልጻሉ፤ ትርጒሙም ይሄው ነው።

59 አሁን፤ ኢየሱስ፤ (ጊዜ ለመቆጠብ)፤ በቅዱስ ዮሃንስ፤ 14ኛ ምዕራፍ፤ 12ኛው ቁጥር፤ ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ "በእኔ የሚያምን ሁሉ፤ እኔ የምሰራውን እርሱ ደግሞ ያደርጋል።" ብሏል አላለም? በትክክል። ይሄ ምንም ትርጓሜ አያስፈልገውም። አንድ ሰው ስራውን ሲሰራ፤ እግዚአብሄር ነው። በትክክል!

60 ደግሞም "በሎጥ ዘመን እንደነበረ፤ የሰው ልጅ በሚመጣበት ዘመንምም እንዲሁ ይሆናል" ብሏል። ኢየሱስ ይሄን ብሏል። ብሏል አላለም? በትክክል፤ ብሏል! ይሄም ትርጒም አይሻም።

"ይሄ ማለትኮ... " ይላሉ፤

61 ማለቱማ እሱ እንዳለው ነው! "በሎጥ ዘመን እንደነበረ፤ በሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል።" በሎጥ ዘምን ምን ነበር? ምን እንደነበረ ለመረዳት፤ ለአፍታ ያህል ወደኋላ እንመለስ።

62 በሎጥ ዘመን ሶስት ዓይነት ሰዎች ነበሩ፤ አማኞች፣ አስመሳይ-አማኞች፣ እና የማያምኑ። በእያንዳንዱ ጉባኤ፤ እንዲሁ ተመሳሳይ ነገር አለ።

የማያምኑ የሚባሉ ሶዶማውያንን እናገኛለን።

ሎጥ ደግሞ አስመሳይ-አማኝ ነበር።

63 አብራሃም አማኝ ነው። ቃል ኪዳን የተደረገለት ለሱ ነበር። የቃል ኪዳን ልጅ ፈላጊ እሱ ነበርና። ሲጠባበቅ የነበረው እርሱ ነው። አሜን። ("አሜን" ያልኩት ስለራሴ አይደለም። **አሜን** ማለት "ይሁን!" ማለት ነው) ደግሞም ትክክል ነው። አብራሃም የዛሬዋ መንፈሳዊት ቤተክርስትያ ጥላ ነው። በሰዶም አልነበረም። አብራሃም የነበረው ከሰዶም ውጪ ከፍ ብሎ ነው።

64 ሎጥ ግን አሁንም በሰዶም እንዳለች የሐይማኖት ተቋም ጥላ ነበር። ተመልከቱ፤ መጽሐፍ ሲናገር፤ "የሰዶም ዓመጽ ጻድቅ ነፍሱ አስጨንቆት ነበር" ይላል። ወጥቶ ለመቃወም በቂ ሐሞት ያልነበረው ለምንድነው? ዛሬም ብዙ መልካም ሰዎች በቤትክርትያን ውስጥ ተቀምጠው፤ ሴቶች አጫጭር ልብሶች ሲለብሱ ወንዶችም ብዙ ነገሮች ሲያደርጉ፤ የጉባኤው አባላት፤ በእሁድ ቀን ቤተክርስትያን ከመሄድ ይልቅ፤ ጎልፍ ለመጫወት ሲሄዱ፣ ዋክ ለማድረግ ወደ ፓርቲዎች፣ ወደ መዋኛ እና ወዘተ ሲሄዱ። ቤተክርስትያን ከመሄድ ይልቅ፤ እሮብ ማታ በቤቶቻቸው ቁጭ ብለው፤ ቴሌቪዥን ሲከታተሉ። የሆነ ነገር ተናገር የሚላቸው ስሜት እያለ፤ ከተናገሩ ግን ቦርዱ ያባርራቸዋል። ችግሩ ምንድነው? አሁንም ሎጥ ነው፤ በመሰኮቱ አሻግሮ ሐጢአያት እያየ፤ ሐጢአትን "ሐጢአት ነው!" ለማለት የሚፈራ።

65 አብራሃም የመንፈሳዊቷ ቤተክርስትያን ጥላ ነው። በነሱ ውጥንቅጥ ውስጥ አልገባም፤ ከዚያ ውጭ ነበር። በዚህ በመጨረሻ ዘመንም፤ እሳት ከመዝነቡ በፊት የሚሆን ነገር ተመልከቱ። እነኚያም አሕዛብ ነበሩ። ዛሬ መንግስታት ሁሉ ተበታትነው የአሕዛብ ወገን በእሳት እንደሚቃጠል፤ የሚያሳይ ጥላ ነው። "ሰማያት ይቀልጣሉ፤" ብሏል ጌታም፤ "በታላቅ ትኩሳት ይነዳሉ።" ያ ማለት የዚህ ጥላ ነበር።

66 እስኪ በሰዕል እናስቀምጠው። አብራሃም ቀድሞ ወጥቷል፤ በሰዶም አልነበረም፤ ከሰዶም ውጭ ነው። ሎጥ ግን በሰዶም ቀርቷል።

67 አንድ ቀን ጠዋት፤ ከቀኑ አምስት ሰዓት ገደማ፤ ባልተለመደ መልኩ፤ ሶስት ሰዎች ሲመጡ አየ፤ በጎዳናው፤ በመንገድ የሚጓዙ፤ ተራ ሰዎች። አብራሃምም ከዛፍ በታች ተቀምጦ፤ አረፍ ብሏል። ምናልባት ከከሰዓት፤ ለመመለስ ፈልጎ፤ ማልዶ ከመንጋው ጋር ሳይወጣ አይቀርም። ድንገት ግን ሶስት ሰዎች ሲመጡ አየ። ሰዎቹ፤ አንዳች የሚያነቃ፤ ልዩ ነገር ነበረበቻው። ኦ፤ ማይ!

68 እግዚአብሔር ሁሌም ለየት የሚያሰብለው አንድ ነገር አለ፤ ህዝቡ ዘንድ ሲመጣ፤ ያነቃቃቸዋል። ያውቁታል። የሆነ ነገር እዚህ ጋር የተገለጠ አለ ብሎ፤ ሹክ ይላቸዋል።

69 አብራሃም ፈጥኖ ተነሳና፤ "ጌታየ፤ ጎራ በልና ጥቂት ውኃ ይምጣላላችሁ፤ እግራችሁን ታጠቡ፤ ቍራሽ እንጀራም ላምጣላችሁ፥ ልባችሁንም ደግፉ፤ ከዚያም በኋላ ትሄዳላችሁ።" ከዛ በኋላ ፊቱን መለሰ። ፈጥኖም ወደ መንጋው ሄዶ ጥጃን አምጥቶ አረደ፤ የሚያበጅለት ባርያም ነበረው። ከሱ በታች ወደነበረው፤ ወደ ድንኳኑ ሄዶ፤ ሳራ አገኛትና ዱቄቱን አዘጋጂች፤ እና፤ ምግብ ነገር፤ ዳቦ ጋገረች፣ በፎርኖ ውስጥም ኬክ አዘጋጅች። አምጥቶም አቀረበላቸው። በዚያ ተቀምጠው፤ እየበሉ ሳሉ፤ አንዳች ነገር አስተዋሉ፤ ይህ ሰው ደጋግሞ ፊቱን ወደ ሰዶም ያደርጋል። እንዲህም አለ...

70 ሁለቱ፤ ወደ ሰዶም እንደሄዱ፤ አስታውሱ። ሁለት ሰዶም ሄዷል። እባካችሁ ይህን አይለፋችሁ። ኢየሱስ የተናገረውን ነውና የምጠቅሰው። ሎጥን እና ለመውጣት የተዘጋጁትን ለማውጣት ሁለቱ ወደ ሰዶም ወረዱ። እነዚያ ሁለቱ ሰዎች፤ ወደዚያ ወርደው ሰብከትን ሰበኩ። (አንዱ ግን ከአብራሃም ጋር እዚያው ቆይቷል። ያረገውን ምልክት ተመልከቱ።) እነሱም እዚያው... የተቀበሉት ምልክት ነበረ ሶዶማውያኖች በዕውርነት ተመቱ። ወንጌል ሲሰበክ ሁሌም የማያምኑትን ሰዎች ዓይን ማሳወር ነው። እናም የተደረገውም አስተውሉ።

71 አሁን፤ አንዱ ከአብራሃም ዘንድ ቀርቶ በፊቱ ምልክትን እያደረገ ነው።

72 አሁን፤ አስተውላችኋል? የትኛውም የታሪክ ምሁር ይሁን፤ ቅዱስ ቃል ይሁን፣ ታሪክ ይሁን መርምሩ፣ በቤተክርስትያን ዘመን ታሪክ በዓለም ወዳሉት ተራ አብያተክርስትያናት የተላከ አንድም ሰው አልነበረም፤ እንደ አብራሃም የሰሙ መጨረሻ ሃ-ም የሆነ አንድ ሰው፤ወደ ሐይማኖት ተቋማት መጥቶ አያውቅም። አሁን ግን ውደዚያ ወርዶ፤ እየተጣራ የሚገኝ፤ ግ-ራ-ሃ-ም የተባለ፤ ሰው መጥቷል። ትክክል ነው። በዚያም ታላቅ ሰራ እየሰራ ይገኛል። ግራሃም፤ ቢሊ ግራሃም፤ በሐይማኖት ተቋማት፣ በፖለቲከኞች፣ ወዘተ መካከል እየሰባበረ ያለ የእግዚአብሔር ባርያ ነው።

73 ባለፈው ግዜ ፕረሲደት ለመሆን ተወዳደር ሲሉት፤ ከልቡ አልፈልግም አላቸው። ለዚህም፤ እግዚአብሄር ይባርከው። እነዚህ ዊስኪ ኩባንያዎች፤ በፍጹም እንደ ድሮው አይሆንላትም ነበር። እነሱም ቢልዮን ዶላሮችን በከሰሩ፤ ለምን፤ በቀላሉ ሊያሸንፋቸው ስለሚችል፤ የሲጋራ ኩባንያዎች እና ሌሎቹም ሁሉ። አያችሁ፤ ትክክል ነው። ለሶዶማውያን እንደተላከ የእግዚአብሄር መልዕክተኛ ወጥቷልና።

74 ነገር ግን አስታውሱ፤ ከአብራሃም ጋር የቀረ፤ ሌላ ሰው ነበረ፤ ሁለቱ አይደሉም እነዚያ ለመሰበክ የወረዱት ዘመናዊ ወንጌላውያን አይደሉም። አንድ ሰው እንደቀረ፤ አስተውሉ። ሁለቱ **በዚያ** ታች ወረዱ፤ አንዱ ደግሞ **እዚሁ** ከአብራሃም ጋር ቀረ። ይህ ከአብራሃም ጋር የቀረውም ምልክትን ሰጥቶታል።

75 ከአንድ ወይም ከሁለት ቀን በፊት፤ አሁን እዩ፤ "አብራም" ይባል ነበር ሚስቱም "ሳራይ" ስትባል ቆይታለች። እግዚአብሄር ተገልጦለት፤ "ስምህ ከአብራም ወደ አብራሃም ቀይሬዋለሁ" ብሎ ነገረው። (አያችሁ፤ G-r-a-h-a-m ሰድስት ፊደል ነው፤ የሰው።) A-b-r-a-h-a-m ግን ሰባት ነው፤ ሰባት ፊደል፤ h-a-m፤ በ h-a-m ይጨርሳል።

76 እዚህጋ፤ በመንፈሳዊት ቤተክርስትያን፤ ከአብራሃም ጋር አንድ ሰው ቀርቷል፤ ምን እንዳለውም ተመልከቱት። "አብራሃም" አለው፤ ("አብራም" አላለም) "አብራሃም፤ ሚስትህ ሳ-ራ-ህ- የት አለች? " (ሳ-ራ አይደለም) "ሚስትህ ሳራህ ወዴት ናት? "

77 ያለውን ተመልከቱት፤ "ከኋላህ በድንኳን ውስጥ ናት።"

78 እሱም እንዲህ አለው፡- "እጎበኝሃለሁ። እኔ እጎበኝሃለሁ።" ግለ ተውላጠ ሰሙን አያችሁት፤ ብቻውን፤ እንደ ተሰፋ ቃሉ የሚያደርግ። እርሱ አምላክ ነው! "እኔ እጎበኝሃለሁ" አለ።

79 ሳራህም፤ (ሁላችንም በሚገባን መልኩ) እጅጌዋን ጎተት አርጋ፤ እየሳቀች፤ "እኔ፤ አሮጊትዋ ሴት፤ ጌታየም፤ (አብራሃምን) አንድ መቶ አመታቸው" አለች፤ "እሱም ሸማግሌ ነው፤ የወጣትነት ጊዜአችን አልፎብናል።" "ከአሁን በኋላ፤ እንደዚያ ዓይነት ስሜት ሊኖረን አይችልም፤ እኔ አሮጊት እሱም ሸምግሏል።" አለች። "እንዲህ ማድረግ አንችልም።" አለች። ደግማም "እንዴት? ይህ ሊሆን አይችልም!" አለች።

80 እና—ያ ሰው (እግዚአብሄር በሰው አካል) "ሳራ እንዲህ እና እንዲያ እያለች፤ ለምን ሳቀች ለምንስ ተጠራጠረች? " አለ። በድንኳኑ፤ ከበስተጀርባው ሆና።

81 አሁን የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት፤ እንዲህ ዓይነት ካልነበረ አስተውሉ! የተሰበሰበውን ህዝብ ተመልክቶ የልባቸውን አሳብ ያውቅ ነበርና። ጴጥሮስ ማን እንደሆነ እና የአባቱ ስም ማን እንደሚባል ነግሮታል። ናትናኤልን ነግሮታል።

82 በውሃው ጉድጓድ ለነበረች ሴትም ነግሯታል፤ ስትናገረው... "ሂጂና የምጠጣው አምጪልኝ፤" ወይም "የሚጠጣ ስጪኝ።" አላት፤

83 እሷም፤ "ጌታየ፤ አንተ አይሁዳዊ ስትሆን... ከሳምራውያን ጋር ለመነጋገ የተለመደ አይደለም። እኛ እና እናንተ የሚያቀራርብ ጉዳይ የለንም" አለችው።

84 እርሱም፤ "ከማን ጋር እንደምትናገሪ ብታውቂ ግን፤ የሚጠጣ ትጠይቂኝ ነበርሽ" አላት። ምልሱ ቀጠለ። "ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ነይ።" አላት።

እሷም "ባል የለኝም።" አለችው።

እሱም "መልካም ተናገርሽ፤ አምስት ባሎች ነበሩሽ።" አላት።

እሷም "ጌታየ!" አለች።

85 በሷ እና በእነዚያ መካከል ያለውን ልዩነት ተመልከቱት—እነዚያ የዘመኑ ክሃናት ፤ በሌላ ዘመን ጮራ የሚኖሩ ሰብሰቦች። "ዲያብሎስ ነው!" አሉት። በሆነ ነገር ላይ ለህብረታቸው መልስ መስጠት ግድ ነው፤ ስለሚያስገድዳቸው።

86 ይህች ትሁት ሴት ያደረገችው፤ ይህ አስቀድሞ የተወሰነ በልቧም ያለው ዘር... በነገሮች ተሰላችታ ደክማለች፤ እንደ ዝሙት አዳሪ በየመንገዱ ሄዳለች። ይሄን ነገር ስታይ ግን፤ "ጌታየ፤ ነብዪ እንደሆንክ አያለሁ፤ አለች። ለአራት መቶ አመታት ያህል አንድም ነብዩ አልነበረንም፤ መሲሑ ሲመጣ ግን እነዚህ ነግሮች እንደሚያደርግ ተነግሮናል" አለችው። ኦ፤ ማይ! በሷ ውስጥ የነበረውን ዘር ህይወት ዘርቶ ዘለለ! ለምን? ምንም ትርጉም አያስፈልገውም።

87 ኢየሱስም፤ "አሁን የማናግርሽ እኔ እሱ ነኝ" አላት። ይህም ተርጓሚ አያስፈልገውም። ተአምር አደረገ መሲሕ መሆኑን መሰከረ፤ አሜን፤ እንደ እግዚአብሄር ቃል ኪዳንም ምስክርን አቆመ ("ጌታ አምላካችሁ እንደ እኔ ያለ ነብዩ ያስነሳላቿል፤" ብሏል ሙሴ)። ይህ ምንድነው? ቅዱስ ቃል ሲገለጥ ነው!

88 ወደ ከተማው ሮጣ ሄደችና፤ እንዲህ አለች፤ "የፈጸምኩት ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩት። እንጃ ክርስቶስ ይህ አይደለምን? ይሄ አይደለም እሱ? የሰራሁትን ሁሉ ነግሮኛል።"

89 አሁን አስተውሉ፤ ይህ በዚያ ሰው አካል ውስጥ የነበረው፤ ይህ ኢየሱስ ጀርባውን ወደ ድንኳኑ አዙሮ ሳራህ በዱንኳን ውስጥ ሆና የምታሰበውን ተናግረ።

90 የእግዚአብሄር ቃል በዕብራውያን 4ኛው ምዕራፍ፤ ላይ... እንዲህ ይላል፤ "የእግዚአብሔር ቃል፤ የሚሠራ፤ ሁለትም-አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፤ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፤ የልብንም ሰሜትና አሳብ ይመረምራል።" ቃል ነው! ነቢይ በመጣ ቁጥር፤ ቃል ይዞ ይመጣል ፣ ለትውልዱም የዘመናቸው ቃል ይሆንላቸዋል። ምን አደረገ? የልብን ሀሳቦች የሚመረምር ነብዪ።

91 ይህ በኢየሱስ ክርስቶስም ተፈጽሟል የቃል ሙላት ስለነበረ።

92 እናም ኢየሱስ "በሰዶም ዘመን እንደ ነበረ እንዲሁ በሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል" አለ። የእግዚአብሔር መንፈስ በሰው አምሳል በምድር ላይ ወረደ፣ እግዚአብሔር በሰው ሥጋ ተገለጦ (አሜን! ተረዳችሁት?) ፣ እግዚአብሔር በሰው አካል ሆኖ ሰዶም ላይ ያደረገውን ያደርጋል። አስታውሱ፤ እነሱም ቃል የተገባለትን ልጅ ሲጠብቁ ነበር። እናም፤ ወዲያው፤ የተስፋው ልጅ መጣ። የተሰፋው ልጅ ከመምጣቱ በፊት የሰዶምና የአብርሃም ቡድኖች ያዩት የመጨረሻ ምልክት ይህ ነበር። አስተውላችሁታል? አሁንም መንፈሳዊትዋ ቤተክርስትያንም ወደዚያች ሰዓት ደርሳለች።

93 አንድ ሰው እንዲህ አለኝ፤ “ወንድም ብራንሃም፤ ‘ያ ሰው እግዚአብሄር ነበረ’ እያልከን ነው? ”

94 መጽሐፍ ቅዱስ፤ አምላክ ነበር ብሏል! ተርጓሚ አያስፈልገውም። ኤሎሂም ነው። አብርሃም የጠራው እሱን ነው። ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢ ያውቀዋል። **ኤሎሂም** ፤ “ሁሉን-ቻይ።” መጀመርያ የነበረ፣ ፍጻሜ፣ መጀመሪያ፣ መጨረሻ። ኤሎሂም! አብርሃም “ኤሎሂም” ብሎ ጠራው። አምላክ (በዕብራይስጥ በካፒታል ለተር) ፣ ኤሎሂም፤ “መጀመሪያ እግዚአብሔር” እንደ፤ ኤሎሂም ነው።

95 እሱ በሰው ሥጋ የተገለጠ፤ የሰው ልብሰ ለብሶ፣ የሰውን ምግብ የበላ ኤሎሂም ነበር። አሜን! ይህም እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን በሰው ሥጋ በሕዝቡ መካከል እንደሚገለጥ ምልክት ነው! አሜን! ኢየሱስ “እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ። በሰዶም ዘመን እንደ ነበረ፤ እንዲሁ በሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል” አለ። አሜን! የሚያስፈልገው መገለጥ እንጂ፤ ትርጉም አያስፈልገውም፤ የሚጠይቀውም ይህ ነው። አሜን። ታምናላችሁ?

ራሶቻችን ዝቅ እናድርግ።

96 የሰማይ አባታችን ሆይ፤ እንደተናገርክ፤ ቃልም እንደገባህ፤ ዛሬ ማታ ቃል ኪዳንህን ወደ አንተ እናመጣለን። ከአንተ በቀር ቃልህን ሕያው ሊያደርግ የሚችል የለም። “ብርሃን ይሁን” ስትል፤ ብርሃንም ሆነ። ስለተከናወነም፤ ተርጓሚ አያስፈልገውም።

97 “ድንግል ትፀንሳለች” ብለን፤ ነቢዩን ኢሳያስ፤ እንደጠቀስነው፤ ጸንሳለች፤ ጸንሳለችና፤ ሌላ ዓይነት ትረካ አያስፈልግም። የሆነው ይህ ነው።

98 እርሱ በመጣ ጊዜ በቤተልሔም ይወለዳል ብለሃል፤ “አንቺ ቤተልሔም፤ ይሁዳ። ከእስራኤል ከይሁዳ አለቆች ሁሉ ታናሽ አይደለሽምን? ነገር ግን ሕዝቤን የሚገዛ ከአንቺ ይወጣል።”

99 የሚያደርጋቸው ነገሮች ፣ በመስቀል ላይ የሚያወጣው ድምጽ፤ እንዴት እንደሚፈረድበት፣ እግሩንና እጆቹን እንዴት እንደሚወጋ ሁሉ፤ “እርሱ ስለ መተላለፋችን ቆሰለ ስለ በደላችንም ደቀቀ፡ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን።”

100 እንዴትስ ዳዊት “ነፍሱን በሲኦል አትተዋትም ፣ ቅዱሴም መበስበሱን ያይ ዘንድ አልፈቅድም” አለ። በሦስተኛውም ቀን ስጋው ለመበስበስ ከመዘጋጀቱ ከሰባ ሁለት ሰዓት በፊት፤ የእግዚአብሔር ቃል፤ “ይነሳል” ብላል። (እነሱ ስጋውን ሰርቀውት ነው አሉ፤ አሁንም ድረስ ያምናሉ።) እኛ ግን፤ ጌታ ሆይ፤ ቃልህን እናምናለን! ተገለጧልና። ኢየሱስ ክርስቶስ ተነስቶ፤ “እነሆ... እኔ፤ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ” ብሏል።

101 ዛሬ ማታ እዚህ እንዳለህ እናምናለን። ልክ ያኔ እንደነበርከው፤ ዛሬም፤ በዚህ ምሽት ያው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆንክ እናምናለን። አሁንም እራስህን ለመግለጥ የሚጠቅሙህን አይኖች፣ እጆች፣ እግሮች፣ አፍ፣ ነፍሶች፣ አካላት ብቻ ትፈልጋለህ። እግዚአብሔር ሆይ፤ ሕያው የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን በመካከላችን እንድናይ፤ ዛሬ ማታ ቀድሰን። እሱ ይምጣ! ከዚያ በኋላ፤ በዚያች

ቀን እንደመጡት “ጌቶች ሆይ፤ ኢየሱስን ማየት እንፈልጋለን” ብለው እንደኋጉ ግሪካውያን ይሆንልናል። እሱንም አዩት። አቤት፤ እርሱን ሲመለከቱት ምንኛ ተደስተው ይሆን!

102 እግዚአብሔር ሆይ ፣ ዛሬም ያው ነህ። ከልብ ከፈለግንህ አንተን ማየት እንደምንችል ቃል ገብተህልናል። “ጥቂት ጊዜ፤ ዓለም አያየኝም” (የማያምን)፣ “እናንተ ግን፤ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር፤ በእናንተም ውስጥ ስለምሆን፤ ታዩኛላችሁ።” ትናንትና፣ ዛሬ፣ ለዘላለምም ያው እንደሆንክ እውቀናል።

103 ጌታ ሆይ፤ ቃሎቹ ተነግረዋል፤ ደግሞም የተጻፈ ነው፤ አሁን ግን ስለ እግዚአብሔር ክብር፤ ይፈጸም፤ ይህም ቃሉን የሚጠብቅ መሆንህን ለማሳየት ነው። አሜን። እግዚአብሄር ይባርካችሁ።

104 አሁን የጸሎት መሰመሩን መጥራት እጀምራለሁ። ቢሊ አሁን እዚህ የለም እንጂ። የጸሎት ካርዶችን፤ ከአንድ እስከ መቶ፤ ወይም እንደሱ ዓይነት፤ ሰጥቻለሁ እንዳለ አምናለሁ። አለ... የጸሎት ካርድ ቁጥሩ ስንት ነው... እስኪ አንድ ሰው ከበሰተጀርባው ይይልኝ... ሊሆን የሚችለው—ቁጥር እና—ፊደል ነው (A, B, C, D, ወይም... )። ምንድነው A ነው? መልካም።

105 እሺ A፤ ቁጥር አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት፣ አምስት። አሁን በዚህ መልኩ መቆም ጀምሩ። A፤ ቁጥር አንድ፣ ቁጥር ሁለት፣ ቁጥር ሶስት፣ ቁጥር አራት። አራት፤ የቆመ ሰው አይታየኝም። የጸሎት ካርድ ቁጥር አራት። አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት። የጸሎት... ምናልባት መቆም የማይችሉ ይሆናሉ። የማይችሉ ከሆኑ፤ እስኪ አጠገባችሁ ያለውን ሰው ካርድ ፈትሹ፤ ካርድ ይዘው መነሳት የማይችሉ ሊሆኑ ስለሚችሉ። በፍጥነት አሁን። ያውና፤ አራት። አምስት ነው፤ የጸሎት ካርድ ቁጥር አምስት። ስድስት፣ ሰባት፣ ስምንት፣ ዘጠኝ፣ አስር፣ አስራ አንድ፣ አስራ ሁለት። ቁጥሮቻችሁ ሲጠራ ወድያው ወደዚህ መምጣት ጀምሩ። ቁጥር አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ በፍጥነት በዚህ በኩል ኑ። የጸሎት ካርድ ቁጥር አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት፣ ስምንት፣ ዘጠኝ፣ አስር፣ አስራ አንድ፣ ቦታችሁን ያዙ። አስራ አንድ፣ አስራ ሁለት፣ አስራ ሶስት፣ አስራ አራት፣ አስራ አምስት፣ አስራ ስድስት፣ አስራ ሰባት፣ አስራ ስምንት፣ አስራ ዘጠኝ፣ ሀያ፣ ሀያ-አንድ፣ ሀያ-ሁለት፣ ሀያ-ሶስት፣ ሀያ-አራት፣ ሀያ-አምስት። የማይችል ሰው ካለ...

106 እዚያ ከኋላ በዊልቼር አንድ ወጣት ይታየኛል። ልጄ፤ ሰምህ ከተጠራ፤ እና—ካልቻልክ... ብቻ፤ እጅህን ከፍ አድርግ፤ ወደዚህ የምትመጣበት እናያለን። አያችሁ?

107 ህመምተኛ ሆናችሁ የጸሎት ካርድ ያላገኛችሁ ስንት አላችሁ እዚህ? ባላችሁበት፤ እጃቻችሁን አሳዩን። እዚያ ጋር፤ አዎን፤ እጅህን ወደላይ ከፍ አድርግ። ታምናለህ? እስኪ እስኪሰበሰቧቸው ድረስ፤ ትላንትናም ለዘለአለምም ያው እንደሆነ፤ ታምናላችሁ? ስንቶቻችሁ? አገልጋዮችን እዩአቸው። ወንድሞቼ፤ ቅዱስ ቃሉ እንዲህ አላለምን፦ ብድካማችን ስሜት ሊነካ የሚችል ሊቀ ካህን እንዳለን ይናገር የለምን? ልክ ነው? ስንቶች ታምናላችሁ፤ እጃችሁን አንሱት? በድካማችን ሰሜት ሊነካ የሚችል ሊቀ ካህን ነው።

108 እንግዲያውስ መጽሀፍ ቅዱስ፦ “ትላንትም ለዘለአለምም ያው ነው” ካለ፤ ሰንቶች ታምናላችሁ? ታድያ ዛሬስ እንዴት እንዴት ያደርጋል? ታላንትና እንዳደረገው ዓይነት ያደርጋል። ልክ ነው? አሁን እሱ የት ነው? በአካሉ ላይ፤ በግርማው ቀኝ ተቀምጧል፤ መንፈስ ቅዱስም እሱን እንዲያስተዋውቅ፤ በህንጻው ውስጥ አለ።

109 አሁን፤ ይሄን አስተውሉ። በሆነ ሰው የልብሱን ጫፍ በተነካ ቀን ምን ሆነ፤ ያቺ ሴት የነካችው ዕለት? ማለት የሚቻለው፤ የጸሎት ካርድ አልነበራትም፤ ነገር ግን ልብሱን ዳሰሰች። ልብሱን በዳሰሰች ጊዜ ግን፤ ኢየሱስ ዞር ብሎ፤ “የነካኝ ማን ነው? ” አለ።

110 ጴጥሮስም፤ እንዲህ በማለት ገሰጸው፤ “እንዴት፤ ጌታ ሆይ፤ ሰው ሁሉ እያጋፋህ። ለምን፡ ይሄ፡ ትርጉም እንኳን አይሰጥም። ‘ማን ዳሰሰኝ’ ለምን ትላለህ? ”

111 እሱም አለ፤ “ሲደክመኝ እየታወቀኝ ነው።” **ሀይል**፤ ማለት “ጉልበት፤” ከእሱ እንደወጣ ሰንቶች ታውቃላችሁ?። “አንድ ሰው በተለየ መለኩ ስለዳሰሰኝ፤ ደከም ብሎኛል አለ።” የዚያን እምነት ሞገድ ከወዴት እንደመጣ እስኪያገኘው ድረስ ወደ ጉባኤው ዞር ብሎ ቃኘ።

112 ሰዎቹ ሁሉ፤ “መምህር ሆይ፤ እኛ እናምንሃለን” እንዲህ እና እንዲያ፤ እያሉ እጆቻቸው ጭነውበታል።

113 አንድ ግን በትክክል ያመነች ሰው ነበረች። እሷም ልብሱን ዳሰሳ መፈወሷን አምናለች፤ እሱን ብትዳሰሰው የሚሆንላት ይህ እንደሆነ በልቧ ተናግራለችና።

114 ፈልጎ እስኪያገኛት ድረስ ፊቱን ወደ ህዝቡ አዞሮ ቃኘ፤ እንዲህ አላት… የደም ችግርሽ ቆሟል ተፈውሰሻል አላት። ልክ ነው? አሁንም፤ በጉባኤ መሃል በህዝቡ መካከል የሚሰራው ይሄው ነው።

115 እያልኩ ያለሁት፤ ህያው እንደነበረ አሁንም ህያው ነው፤ አልሞተም እያልኳችሁ ነው። መጽሀፍ ሲናገር፤ ኢየሱስ ራሱ፤ ሲናገር፤ “በሰዶም ዘመን እንደ ነበረ እንዲሁ በሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል።”

116 አሁን ተመልከቱ፤ እግዚአብሔር ምንም ያህል ጸጋ ቢኖረውም፤ አቤት የሚል ምላሽ የሚሰጥ፤ ሌላ፤ እዚህ ሊኖር ግድ ነው። መጽሐፍ ሲናገር፤ ወደ ከተማ እንደገባ፤ “ባለማመናቸው ጠንቅ ግን ማድረግ ያልቻለው ብዙ ነገሮች እንደ ነበሩ” ይነግራል። ልክ ነው? ዛሬም ያው ነው። ልታምኑት ያስፈልጋል። በቃ ልታምኑት ግድ ነው። ብቸኛው መንገድ ይሄው ነው።

117 የጸሎት መስመሩ ተዘጋጅቷል? አሁን፤ ሁላችሁም ለአስር ደቂቃ ያህል በመንፈስ ሁኑ። ሁሉንም አዳርሳለሁ ለማለት እርግጠኛ አይደለሁም፤ ሀያ-አምስት እስከ ሰላሳ ያህል ቆሟል። አሁን ግን በጸሎት መስመር፤ እኔ ለእናንተ እንግዳ መሆኔን የምታውቁ እያንዳንዳችሁ በጸሎት መስመሩ ውስጥ ያላችሁ፣ እኔም ስለእናንተ አንዳች የማላውቅ፤ እጆቻችሁን ከፍ አድርጉት። በጸሎት መስመር ያላችሁ እያንዳንዳችሁ።

118 በጉባኤው መካከልም፤ ስለእናንተ አንዳች እንደማላውቅ የምታውቁ ሁላችሁ፤ እጆቻችሁ ከፍ አድርጉ። እያችሁ ወዳጆቼ፤ አሁን፤ ማለት የፈለግኩት ይህ ነው። በቃ፤ ይሄው ነው። አገልጋዮች ሁሉ በመድረክ ናቸው። ክርስቶስ

ደግሞ ቃል ገብቷል። አያችሁ፤ ተጽፏል ተብሏል። የሚፈጸመውስ መቼ ነው? ጌታ ኢየሱስ ከመምጣቱ፤ ከመጨረሻዎቹ ቀናት በፊት። ልክ ነው? ያኔ ሊፈጸም ነበር።

119 አሁን፤ ዛሬ የተነገረው ትንቢት ይህ ነው። የሉተር ብርሃን አይደለም፣ የዌስሊ ብርሃንም አይደለም፣ እንዲሁም የጴንጤቆጤዎች ብርሃንም አይደለም። አልፎ መንገዱን ቀጥሏል። አሁን፤ ሉተራን ብትሆኑ ችግር የለውም፣ ሜተዲስት ችግር የለም፣ ባፕቲስት ችግር የለም፣ ሁሉንም፣ ጴንጤቆጤዎች፣ ደህና። ከሁሉም አይነት እዚህ ተቀምጧል ዛሬ። ግለሰብን አይደለም— ግለሰብን አይደለም—አይደለም። እንደዛ ቢሆን ኖሮስ...

120 እንደ ሜተዲስትን ስለ ሉተር ለመናገር ፈጽማችሁ ባልቻላችሁ ነበር፤ ምክንያቱ እሱ በቅድስና የሚያምን ነበር ሉተር ግን እንደሱ አይደለም። አያችሁ?

121 አንድ ጴንጤቆስጤ የጸጋ ስጦታዎች መቃናት ሰላየ፤ "መደምደምያው ቅድስና ነው" ልትሉት አትችሉም። ይሄን አያምንም። ከዚያ ይልቅ ከፍ ያለ ነገር ሰላየ፤ አያምንም። አያችሁ? ያውም ደግሞ ያለነው የመጨረሻው የቤተክርስትያን ዘመን ይህ ነው፤ ሌላ የቤተክርስትያን ዘመን እንደማይኖር መጽሐፍ ተናግሯል።

122 ይሁን እንጂ የህዝቡ መሰብሰብ ይቀጥላል፤ አያችሁ፤ ይሄው እኛም አለን። አሁን፤ የመጨረሻውን ምልክት፤ አስታውሱት። የኪዳን ወንድ ልጅ የምንጠባበቅ ሰዎች ነን? እጃችሁን ከፍ አድርጉ። በክርስቶስ ውስጥ በመሆን የአብራሃም ዘር እንደሆናችሁ ታምናላችሁ? እጃችሁን ከፍ አርጉ። እንግዲያውስ፤ እናንተ የአብራሃም ዘር፤ ምልክቱን ተቀበሉ! በባቢሎን አይገኝም፣ በሐይማኖት ተቋማት ውስጥ የለምና። እናንተ በዚያ ባለው በብልሽት ውስጥ የማትኖሩ፤ እዚሁ ከእናንተ ጋር ነው። እመኑት!

123 ይህች፤ በኔ እድሜ ክልል ውስጥ ያለች ሴት፤ ለእኔ ፍጹም እንግዳ ናት። ይህችን ሴት በዘመኔ አይቻት አላውቅም። ህመምተኛ ከሆነች፤ እሷን መፈወስ ብችል፤ አደርገው ነበር። እኔ ስለሷ ምንም አላውቅም። ከአፍታ በፊት እጇን ስታውጣ አይታችኋታል? እኔ—እሷን አይቻት አላውቅም። ለኔ እዚያ የቆመች ሴት ናት።

124 ዛሬ በዛ ያለ የጸሎት ካርዶችን ይዘው መጥተው፤ ሙሉውን አቀላቅለው ለህዝብ አከፋፍለውታል። አንደኛው እዚህ ጋር ቁጥር አንድ ያገኛል፤ ቁጥር አሰር እዚያ ከኋላ፤ ቁጥር አሰራ አምስት፣ ቁጥር ሰባት፣ ቁጥር... በዚህ መልኩ። ሁሌም፤ በእናንተ ፊት፤ ሁሉንም ይቀላቀላል። ከዚያ በኋላ ሲጠሩ፤ ከየአቅጣጫው ከሁሉም ይጠራል። አያችሁ? አሁን፡ ደግሞ፡ የጸሎት ካርድ መያዝ እንኳን አይጠበቅባችሁም፤ ብቻ እዚያ ቁጭ ብላችሁ እመኑ። ለምን አይሆንም...

125 ዛሬ ማታ፤ እራሳችሁን ቆንጠጥ አርጉና፤ ያለንበትን ዘመን መርምሩት። አያችሁ? ወዳጆች፡ አሁንኮ፡ ሊያበቃ፡ እጅግ ተቃርቧል። በቃ ሊያበቃ ነው!

126 እንግዲህ፡ የአብርሃም አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሙታን ካስነሣው፤ ኢየሱስም በመጨረሻ ዘመን የአብራሃም አይነት ያ መልአክ (ማለት በሰው ስጋ የነበረው እግዚአብሄር) የተሰፋውን ቃል ከመድረሱ ቀደም ብሎ፤ በአብራሃም

ፊት ተመሳሳይ ምልክት... እንዳደረገ፤ ኢየሱስ አሁንም ያንን ተመሳሳይ ነገር ይሆናል እያለን ነው።

127 አሁን፡ አቶሚኮቹ እና የሐይማኖት ተቋማት፣ እና ወዘተ፤ እንዲሁም የገቡባቸው ውጥንቅጦች አይተናል። ቢሊ ግራሃምን፤ እና ኦራል ሮበርትስን፤ ሌሎቹም ሰዎች በዚያ ማዶ የገቡባቸውን ሁሉ አይተን፤ የጴንጤቆስታል መልዕክተኞች እና የድርጅት መልዕክተኞችን ሁሉ፤ ያንን ምልክት ይዘው፤ ሰጓዙ እያየን ነው። ቢሊ ግራሃም፤ ጥርት ያለ የሰነመለኮት ሰው፤ ድርጅቶች የሚያምኑበትን። ኦራል ሮበርትስ፤ ጥርት ያለ ፈዋሽ፤ ልክ የጴንጤቆስጤዎች...

128 እዚህ ግን ተመልከቱ፤ ለአብራሃም ዘር የተገባችለት የሆነች ኪዳን አለች። እነዚያ በተቋሞች መካከል በዚያ ናቸው፤ በተቋሞቹ **ዘንድ ልት**ሆን ያለች አንዳች ነገር አለች፤ ህዝቡን መሰብሰብ። እስከ ነገ ማታ እንለቀዋለን።

129 እዩ፤ ይህች ሴት እኔ አላውቃትም። ጀርባየን ወደሷ አዞራለሁ። ምናልባት በግል ጉዳይ—ወይም በገንዘብ ጉዳይ፤ ጌታ ለዚች ሴት አንዳች ነገር ቢናገራት፤ ህመምም ሊሆን ይችላል፣ እኔ አላውቅም። እውነትም ይሁን ስሕተት እሷ ትመረምራለች።

130 ያኔ ያደረገው አይነት ዛሬም ተመሳሳይ ነገር ካደረገ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻው ዘመን ይመጣል ያለው አምላክ እዚህ እንዳለ ታምኚአለሽ? አሁን እኛ እንደ ሰዶም እየኖርን እንዳለን፤ ዓለም በሙሉ ወደ ሰዶማዊ ሁኔታ እየገባ እንዳለ ስንቶች ታምናላችሁ? ዛሬ ማታ የነገርኳችሁ እውነት እንደሆነስ ስንቶች ታምናላችሁ? እንግዲያውስ፤ እናንተ የአብራሃም ዘር እና ልጆች፤ እግዚአብሄርን እመኑት!

131 አሁን፤ ሴቲቱን ፊት ለፊት እያየኋት አንድን ነገር ለማለት ብሞክር በአይምሮአችሁ፤ የሚመላለስባችሁ ነገር ይመጣል፤ ወይም ስለ ቴሌፓቲ ማወቅ የምትፈልጓቸው የተለያዩ ነገሮች። ስለ ቴሌፓቲ እውቀት ያለው ሰው ከዚያ የተሻለ ስሜት ያለው ሊሆን ይገባል። አያችሁ? አያችሁ? ቴሌፓቲስት ወንጌልን ሲሰብክ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ወይስ ድንቆችን እና ምልክቶችን እያደረገ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ያው መሆኑን እያወጀ፤ ወንጌልን የሚሰብክ መናፍስታዊ ሰው አይታችሁ ታውቃላችሁ?

132 አያችሁ፥ ዝም ብሎ... የሰው ሐሳብ ነው። አያችሁ፤ እውር ናቸው። እውራን ሊሆኑ እንደሚችሉ ታምናላችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይሆናሉ ይላቸዋል። ልክ ነው? "ችኩሎች፤ በትዕቢት የተነፉ፤ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ፤ በኪዳን የማይጸኑ፣ ሀሰተኛ ከሳሾች፤ ራሳቸውን የማይገዙ፤ መልካም የሆነው የማይወዱ፣ የአምልኮት መልክ ያላቸው ኃይሉን ግን የካዱ።"

133 ኢየሱስ በማቴዎስ 24:24 ላይ፤ ስለ ሁለቱ መንፈሶች በመጨረሻው ዘመን፤ የሚቻል ቢሆን ኖሮስ፤ የተመረጡትን እስኪያስቱ ድረስ ይደርሳሉ አላለምን? አይቻልም እንጂ። በመጀመርያ በእግዚአብሄር በሀሳቡ ዘንድ የነበሩ ናቸው፤ የእግዚአብሄር አንድ ክፍል ናቸው።

134 አሁንም፣ የአብርሃምና ፣ የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ፣ ስለ አንተ እውነቱን የምናገር መሆኔ ዛሬ ማታ የታወቀ ይሁን። አንተ ነህ፤ ጌታ ሆይ። አገልጋዮችዎ የራሳቸውን ሀሳብ በትህትና ከመንገድ ያሰወግዱ፤ ሰውነታችንን ስለክብርህ መጠቀም ትችል ዘንድ። በእግዚአብሔር ልጅ፤ በኢየሱስ ስም። አሜን።

135 ስጦታ ምንድነው? ተነስቶ የሚከተፍ እና የሚዞር ነገር አይደለም። አይ፤ አይ። እግዚአብሔር አንተን መጠቀም እንዲችል እራስህን ከመንገድ ገለል ማድረግ ማወቅ ነው። ስጦታ እራስህን ማግለል ብቻ ነው፤ ከዛ በኋላ እግዚአብሄር ይጠቀምበታል።

136 ይህች ከጀርባየ ያለች እመቤት አሁን ካልተፈወሰች ሟች ናት። ይህች ከኋላየ ያለችው እመቤት፤ በቅርብ ጊዜ በሌላ ሰው ተጸልዮላታል። ካንሰር አለባት። ካንሰሩም በጡቷ እና በሳምባዎቿ ላይ ነው። እና በቅርብ ተጸልዮላታል፤ እሷም መፈውሷን በእምነት ለመቀበል እየጣረች ትገኛለች። ጌታ ሰራዊት እንዲህ ብሏል! ልክ ነው፤ እመቤት? [ሴቲቱ፤ “አዎ፡ በትክክል እውነት ነው” አለች።—አርታዒ።] ከሆነ፤ እጅሽን ለጉባኤ አወዛውዢው—አወዛውዢው። የአብራሃም አምላክ ዛሬም ህያው ነው! መልካም፤ ያመንሽውን እያመንሽ ሂጂና ትፈወሺያለሽ። አሜን።

ታምኚአለሽ? አንቺም ብለሻል። “ስለ ጉባኤውስ? ”

137 በመስመሩ መጨረሻ... ከሷ ጋር የተቀመጠችው ሴት፤ እዚያ ጋር ያለች ሁለተኛዋ ሴት። ልክ ወደዚያ ዞር ስል፤ በክንድዋ ዙሪያ የሆነ ነገር አየሁ፣ የደም ግፊት ሲመታ አየሁ። ከፍተኛ የደም ግፊት አለባት። ልክ ነው፤ እመቤት? እጅዎን ከፍ ያድርጉ። ካመኑ የደም ግፊትዎ ይቀንሳል። የአብርሃም አምላክ አሁንም በቦታው ነው። የእግዚአብሔር ቃል ለዚህ ዘመንም፤ ልክ እንደ ድሮው ነው!

138 እንዴት ነሽ? ታምናለሽ? በእግዚአብሔር እምነት ይኑርሽ! ወጣት እመቤት፤ እኔ´ጃ፤ እግዚአብሄር ያውቃል ልብሽን። ህጻን ልጅ ይመስላል። እግዚአብሔር ችግሩን ሊገልጥልኝ እንደሚችል ታምኚያለሽ? መግለጥ ብችል ታምኚዋለሽ? ስለ አንቺ አይደለም፤ ለሌላ ሰው ነው፤ ወንድምሽ ነው። እጅግ አጣብቂኝ ውስጥ ነው፤ በዚህ በስሜን በኩል ባለች ከተማ፤ በቱለር ነው። የሉኪምያ ህመምተኛ ነው፤ አሁን ያለው በሆስፒታል ነው፤ ዶክተሮች ተስፋ ቆርጠው ለሞት ሰጥተውታል። ምንም ተስፋ የለውም። ልክ ነው። ታምኚያለሽ? [ሴቲቱም፤ እያለቀሰች፤ “አዎን” አለች።—አርታዒ።] መልካም። በእጅሽ ምን ይዘሻል? እሱን ውሰጂና በላዩ ላይ አኑሪው። እመኚ! እንዳትጠራጠሪ። አሜን።

139 ታምናላችሁ? ሴቲቱን በህይወቴ አይቻት አላውቅም። እግዚአብሄር ሁሌም እግዚአብሄር ነው! እስኪ አሁን፤ ንገሩኝ ሰው እንዲህ ማድረግ ይችላል? ይህን ለመስራት የሰው ቁመና እንዲህ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻዎቹ ቀናት እዚህ እንደሚሆን ቃል የገባው አምላክ ነው። እና በሰዶም ዘመን እንደነበረው እራሱን (በአብርሃም ዘር ፊት) እራሱን ሊገልጥ ያለው አምላክ።

140 አሁን እዚህ፤ ይቺን ሴት አላውቃትም፣ አንዳችን ለሌላው እንግዳ ነን፤ በህይወት ለመጀመሪያ ጊዜ እንደተያየን እገምታለሁ። ባርያው እንደሆንኩ ታምኚኛለሽ? [እመቤቲቱ፤ “አዎን” አለች።—አርታዒ] ይህስ ቃል መሆኑን ታምኚያለሽ? [“አዎን።”] ይህን የምታውቂ ከሆንሽ... አሁንም ይህ ቃል ስሜትንና የልብን ሐሳብ መርማሪ ነው። ልክ ነው? [“ልክ ነው።”] ማመን ከቻልሽ፤ ቃሉ፤ ፈዋሽ ጭምር ነው። እምነኛል። አንቺም፤ ጥቁር ጥላ፤ አጥሎብሻል። ካንሰር ነው። ካንሰሩ ምንሽ ውስጥ እንዳለ እግዚአብሄር ሊነግርኝ እንደሚችልም ታምኚያለሽ? ዶክተሮች እንዳሉት፤ በታችኛው

እንጀትሽ ነው። እንደምትፈወሺ አሁን አመንሽ? [“አሜን።”] ሂጂ፤ ፈጽመሽ አትጠራጠሪ፤ ጌታ ይፈውሰሻል። አሜን።

141 ሁላችሁ፤ አምናችኋል? ልክ እሱ አደርጋለሁ እንዳለው! በጌታ እምነት ይኑራችሁ፤ አትጠራጠሩ።

142 እንዳችን ለሌላው እንግዳ ነን። እኔ አንቺን አላውቅሽም። እንግዶች ከሆንን፤ እጆቻችን እንደተጨባበጥን፤ በጉባኤው የታወቀ ይሁን። ይህች ሴት በጭራሽ አይቻት አላውቅም።

143 እዚያ ማዶ ላይ ታምናላችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ አምናቿል? ምንድነው? ቃሉ ነው። ሰዎቹ ሲቃወሙት፤ ሰውየውን አይደለም የተቃወሙት፤ ቃሉን ነው የሚቃወሙት። ወደ ውጭ የወጣው ቃሉ ነው፤ ተመልሶ ሊገባ አይችል።

144 አሁን፤ ይቺ ሴት ለኔ እንግዳ ናት። በህይወቴ ሁሉ አይቻት አላውቅም። የሚፈውሰ እግዚአብሄር ነው። ምናልባት ለፈውሰም ላይሆን ይችላል፤ ሌላም ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን እግዚአብሄር ችግርሽ ምን እንደሆነ ለእኔ ከገለጸለኝ፤ ታምኚኛለሽ? እንዲጸለይልሽ የፈለግሽው የመጀመርያው ነገር፤ እጅግ የተጎዳ ጀሮ፤ ሰላለሽ ነው። አንደኛው ጀሮሽ፤ ፈጽመሽ አትሰሚበትም። እውነት ነው። ልክ ነው። ሌላም ሱሰ አለብሽ፤ ሲጋራ የማጨሰ ሱሰ ነው፤ ያንን ሱሰ እንዲወገድልሽ ትፈልጊአለሽ። ጣትሽን በጤነኛው ጀሮሽ ላይ አድርጊ፤ መልካም፤ በጤነኛው ጀሮሽ። መልካም። አሁን እግዚአብሔርን እመኚ እና መንገድሽን ሂጂ፤ እንዳትጠራጠሪ... ካመሽ ከአሁን በኋላ ፈጽመሽ ሲጋራም አታጤሽም። ጌታ ይባርክሽ፤ ሂጂ።

የሆነውን አይታቿል። ህያው አይደለም ታድያ?

145 እኔ አንቺን አላውቅሽም፤ እንዳችን ለሌላው ፍጹም እንግዳ ነን። በዘመኔ አይቼሽ አላውቅም፤ ጌታ ግን ያውቅሻል። እግዚአብሄር ሰለ አንቺ አንዳች ነገር ቢነግረኝ፤ ታምኛለሽ?

146 ጉባኤው በሙሉ ያምናል? ይህችን ሴት የሚያውቃት ሰው ካለ? በጉባኤ ውሰጥ ይህችን ሴት የሚያውቅ ሰው አለ? በጣም ጥሩ፤ ይህ ውሸት ወይም እውነት ከሆነ አንተ ታውቃለህ። ይህ ይደመድመዋል። ይሄ እውነቱን ይገልጣል።

147 አሁን ባለፉት ጥቂት ደቂቃዎች ውሰጥ ምን እንደ ሆነ ማየት ችላቿል። አያችሁ? እያንገዳገደኝ ነው። እንዲህ ነው... አያችሁ? አያችሁ፤ ልብን ሰመረምር። ነገር ሁሉ ጨለምለም እያለብኝ ነው። አያችሁ፤ እኔ አይደለሁም። መንፈሰ ቅዱሰ ነው። ለዚህ ዘመን የተሰጠ የተሰፋ ቃል ነው። ከሐዋርያት ዘመን ወዲህ በጭራሽ አልነበረም፤ ሆኖም አያውቅም። ነገር ግን ለመቼ ነበር የተባለው፤ “የሰው ልጅ ከመምጣቱ ቀደም ብሎ። በሎጥ ዘመን እንደ ነበረ፤ እንዲሁ በሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል።” የማያምኑ አያምኑትም። እነሱ እንዲያምኑ አይጠበቁም። አማኞች ግን ያምኑታል!

148 አሁን መንፈሰ ቅዱሰ ይህንን ከገለጠ፤ ሰንቶች በሙሉ ልባችሁ ታምናላችሁ፤ እጃችሁን ከፍ አድርጉልኝ?

149 አንቺ የደረሰብሽ ጉዳት አለ። የመኪና አደጋ ገጥሞሻል፤ የተወሰኑት ሸርተብሪያዎች ከአንገትሽ ተላቀዋል። በተጨማሪም ኩላሊትሽ ከቦታው ለቋል። ልክ ነው፤ አይደል'ዴ? [ሴቲቱም፤ "አዎን፤ ጌታየ" አለች።—አርታዒ] አምነሻል? ["አዎን፤ ጌታየ።"] ጌታ ይባረክ። ደህና ትሆኛለሽ።

150 እግዚአብሔር የኩላሊትን ህመም እንደሚፈውስ ታምኚአለሽ? እንግዲያውስ ሂጂ ፈውስሽም ተቀበይ።

151 ነይ፤ እመቤት። ወደዚህ ተመልከቺ። እግዚአብሄር የልብን ህመም እንደሚፈውስ ታምኛለሽ? በጣም ጥሩ፤ እመኚና መንገድሽን ሂጂ፤ ልብሽም ጤነኛ ይሆናል።

152 ና ውደዚህ። ጌታ ጀርባህን እንደሚፈውስ፤ ደህና እንደሚያደርግህ ታምናለህ? በል ቀጥል እና እመን።

ብቻ እግዚአብሄርን እመኑ፤ ከእናንተ የሚጠበቅ እሱ ብቻ ነው።

153 ነይ፤ እመቤት። ጌታ የሆድ ህመም እንዲፈውስ ታምኛለሽ? ሂጂ፤ እራትሽኝ ብዪ፤ በሙሉ ልብሽ እመኚ።

154 ነይ። ጌታ አርቲራተስ እንዲፈውስ ታምኛለሽ? በይ ሂጂ፤ እመኚ፤ እንዲሁም... እግዚአብሔርም ይፈውስሻል።

155 በጣም ጥሩ፤ ና። በሙሉ ልብህ ታምናለህ? አምነሃል? አርቲራይተስ፤ እንደገና። ጌታ ሊፈውስህ እንዲችል ታምነዋለህ? በል ቀጥል፤ እመን፤ "ጌታ ሆይ፤ አመሰግንሃለሁ" በለው።

ስንቶች ታምናላልችሁ እዚያ ጋር? አምናችኋል?

156 እዚያ ጋር ቀይ ቀሚስ ለብሰሽ የተቀመጥሽው ሴት፤ እጇን እንዲህ ከፍ ያደረገችው፤ በከባድ ደም ግፊት ስቃይ ላይ ናት። እግዚአብሄር ደህና እንዲያደርግሽ ታምኚዋለሽ? ታምኛለሽ? በጣም ጥሩ። እጆችህን እዚያው ከጎንህ ባለችው ሴት ላይ አኑራቸውና፤ ድምጿ ደህና እንደሚሆንላት ንገራት። አሜን።

ይሄው እንዲህ ነው። አሜን። አምነሻል? እምነት ይኑርሽ!

157 እዚያ ጋር የተቀመጠው ሰው፤ በውስጥ ሰውነቱ ደም ይፈስበታል። እዚህ ጋር የተቀመጥከው፤ ታምናለህ፤ የተከበርክ? አዎን፤ ደም የመፍሰስ ችግር አለብህ። እንደሚድን ታምናለህ?

158 ከጎንህ ያለች ሴትም ደም ይፈስባታል፤ የጀርባ ችግርም አለባት። እግዚአብሔር እንደሚፈውሳችሁ ታምናላችሁ? አምናቿል? እጆችሁን ከፍ አድርጉ እና ተቀበሉት። እመን።

159 ይህች ከጎንህ ያለችው ሴት እግሯ እና ዳሌዋ ላይ ችግር አለባት። እውነት እንደሆነ ታምኛለሽ፤ እመቤት? እንደምትፈወሺ ታምኛለሽ? መልካም፤ እጅሽኝ አንሺና፤ "ተቀብያለሁ" በዪ።

160 በጣም ጥሩ፤ ከሷ ቀጥላ ያለች ሴት ኢንፌክሽን አለባት። መነጽር የለበሰች ወጣት እመቤት፤ እግዚአብሔር ኢንፌክሽኑን እንደሚፈውስ ታምኛለሽ? እጅሽን ወደ ላይ አንሺ፣ እንዲህ፤ "ተቀብያለሁ" በዪ። በጣም ጥሩ፤ እመኚ።

161 አጠገቧ ያለችው እመቤት የኩላሊት ችግር አለባት። እመቤት እግዚአብሔር የኩላሊቱን ችግር ይፈውሳል ብለው ያምናሉ? መልካም፤ እጅዎን ወደ ላይ ያንሱና፤ ይቀበሉት።

162 ከጎኗ ያለችው ትንሽ ልጅ የእንቅርት በሽታ አለባት። እግዚአብሄር እንቅርቱን እዚያው እንደሚፈውሰው ታምኛለሽ? እጅሽኛ ከፍ አድርጊና፤ ተቀበዪው።

163 ሰንቶች በሙሉ ልባችሁ ታምናላችሁ? በእግሮቻችሁ ቁሙና ተቀበሉ። በአብርሃም፣ በይስሐቅና፣ በያዕቆብ አምላክ ፊት ተነሱ።

164 በጌታ በኢየሱስ ክርሰቶስ ሰም መንፈሰ ቅዱስ አሁን በህንፃው ውሰጥ ይውረድና እያንዳንዱን ሰው በመለኮታዊ መገኘት ይፈውሰው!

**እግዚአብሔር የራሱ ተርጓሚ ነው** AMH64-0205

(God Is His Own Interpreter)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ የካቲት 5፡ 1964፡ እሮብ ማታ፡ በካሊፎርኒያ፡ ቤክርሰፊልድ፡ በሚገኝ ኬርን ካውንቲ ፌርግራውንድስ፡ U.S.A፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2021 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

# የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org